## 118ኛው የግብጽ ፓትርያርክ

117ኛው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ታላቁ አባት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ ሲያርፉ ዓለም በሙሉ ነበር ኀዘኑን የገለጠው፡፡ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ፣ ቡድሂስቱና ሺንቶይስቱ፣ የሚያምነውና የማያምነው፣ የቻይናና የአሜሪካ ፖለቲከኞች፣ አንድ ሆነው በአቡነ ሺኖዳ ዕረፍት አዝነው ነበር፡፡

የእርሳቸውን ዕረፍት ተከትሎም የግብጽ ቤተ ክርሰቲያን እንዲህ ዓለምን በፍቅር አንድ አድርገው የሚገዙ ሌላ አባት ታገኝ ይሆን? የሚለው ጥያቄ ግብጻውያን ምእመናንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ያሳሰበ ነበር፡፡ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ዝግጅቷን ጀምራለች፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የአዲስ ፓትርያርክ አመራረጥ ሥርዓት እጅግ የሚያስደስት፣ ለክርክርና ለሐሜት በር የሚዘጋ፣ አባቶችንና ምእመ ናንን የሚያሳትፍ፤ መንፈሳዊነቱንም የተሞላ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ የአዲስ ፓትርያርክ አመራረጥን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ ዝርዝር ሕግ አላየሁም፡፡ በሕገ ቤተ ክርስቲያኑ ላይ ያለው እጅግ በጣም አጭር ነገር ነው፡፡ ሂደቱን፣ የአባቶችንና የምእመናንን ተሳትፎ፣ የእጩ አቀራረብና አመራረጥ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሂደትን የሚያሳይ ራሱን የቻለ ሕግ ያለ አልመሰለኝም፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ አንዱ አከራካሪ ሆኖ የሚታየው ነገር የፓትርያርክ አመራረጥና አሿሿም ጉዳይ ነው፡፡ ከመጀመርያው ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ ጀምሮ ከፖለቲካ ነጻ የሆነ፣ የሕዝቡን አመኔታ ያተረፈ፣ ሕዝቡም እግዚአብሔር አባት ሰጠን ብሎ እንዲያምን የሚያደርግ አሠራር ባለመኖሩ፣ ሐሜቱና ቅሬታው፣ ተቃውሞውና አለመግባባቱ እንዲቀጥል አድርጎታል፡፡

በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ ሌሎች አባቶች፣ አገልጋዮችም ሆኑ ምእመናን ሊያስቡባቸው ከሚገቡ ቤተ ክርስቲያናዊ ጉዳዮች አንዱ የፓትርያርክ አመራረጥና አሿሿም ሥርዓት ነው፡፡ ዛሬ በመንበሩ ላይ ያሉት አቡነ ጳውሎስም ሆኑ ተሰድደው በአሜሪካ ያሉት አቡነ መርቆሬዎስ ማረፋቸው አይቀርም፡፡

ያን ጊዜ አዲሱን አባት እንዴት ነው መምረጥ ያለብን? የእግዚአብሔርንስ ፈቃድ እንዴት እናገኛለን? ከፖለቲካዊና ሌሎች ተጽዕኖዎች ነጻ የሆነ፣ ሁሉንም የሚያግባባ ምርጫ እንዴት ማድረግ ይቻላል? ቅሬታዎችንና ነቀፌታዎቸን እንዴት ማስተናገድና መፍታት ይቻላል? መራጮች እነማን ናቸው? መራጮችስ እንዴት ይመረጣሉ? ለፓትርክና ዕጩ መሆን የሚችሉት እነማን ናቸው? ምን ምን መመዘኛ ያሟሉ ይወዳደራሉ? የሚሉትና ሌሎች በዝርዝር ተደንግገው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ሁሉ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡ አሠራራችን ሁሉ እንደ ሐበሻ መድኃኒት ተደብቆ የሚኖርበት አሠራር እየኀዳን ነው፡፡ ሌላ ጭቅጭቅ ደግሞ ለትውልድ እንዳናተርፍ፡፡




www.danielkibret.com

ግብጻውያን ጠንካራ የምእመናን ጉባኤ ለማግኘት ከ1874 ዓም ጀምረው ለሰባ ዓመታት ታግለዋል፡፡ እና ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን ማሰብ የምንጀምረው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ሲጀምር ነው፡፡ ዘላቂ በሆነ መልኩ እንዴት ችግሮችን እንደምንፈታ አንወያይም፡፡

ለዛሬ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የአዲሱን ፓትርያርክ አመራረጥ ሂደት ግልጽ ለማድረግ ያወጣችውን ጋዜጣዊ መግለጫና ሌሎችንም መዛግብት መሠረት አድርጌ በእነርሱ ዘንድ የአዲስ ፓትርያርክ አመራረጥ ሕግና ሂደት ምን እንደሚመስል ለምሳሌነት ላቅርብ፡፡ «መልክ ከፈጣሪ ሞያ ከጎረቤት» ይባላል፡ እኛም ለእኛ እንደሚሆን አድርገን ብንቀስመው አይጎዳንም፡፡ እንዴት ሁልጊዜ የሰው እያደነቅን እንደተመኘን ብቻ እንቅር፡፡

በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ፓትርያርክ አመራረጥን ሂደት በዝርዝር የሚያስረዳ ራሱን የቻለ ሕግ አለ፡፡ ይህ ሕግ በቅዱስ ሲኖዶሱ ተወስኖ በግብጽ ፓርላማ እኤአ በ1957 ዓም የጸደቀ ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሠረት አንድ ፓትርያርክ ባረፈ በሰባት ቀናት ውስጥ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጳጳሳት መካከል ቀዳሚ የሆነው ሜትሮፖሊታን ዐቃቤ መንበር ለመምረጥ የቅዱስ ሲኖዶሱን አባላት ስብሰባ ይጠራል፡፡ በዚህም መሠረት የአሲዩቱ ሜትሮፖሊታን አቡነ ሚካኤል ይህንን ስብሰባ እንዲያካሂዱ ሜትሮፖሊታን ጳኩሚስን ወከሏቸው፡፡

ይህ ስብሰባ በሁለት አካላት መካከል የሚደረግ ስብሰባ ነው፡፡ በነገራችን ላይ የግብጽን ቤተ ክርስቲያን የሚመሯት ሁለት አካላት ናቸው፡፡ የመጀመርያው በሃይማኖታዊና ሌሎች ጉዳዮች የመጨረሻውን ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው ቅዱስ ሲኖዶሱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ላይ የሚሠራው የምእመናን ጉባኤ (*Al-Maglis al-Milli*) ነው፡፡ የምእመናን ጉባኤ ከ1874 ዓም ጀምሮ በልዩ ልዩ መንግሥታዊ፣ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ አገልግሎታቸው በታወቁ ምእመናን አማካኝነት በቤተ ክርስቲያኒቱ የምእመናንን መብት ለማስጠበቅ፣ ምእመናን በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደርና አገልግሎት ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ ሲታገል የቆየና በመጨረሻም መጀመርያ በአቡነ ቄርሎስ በኋላም በአቡነ ሺኖዳ ጊዜ ይበልጥ የተጠናከረ ጉባኤ ነው፡፡ ይህ የምእመናን ጉባኤ በማናቸውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳዮች ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ጉባኤ ነው፡፡

ሜትሮፖሊታን ሚካኤል የእነዚህ ሁለቱን አካላት ጥምር ጉባኤ መጋቢት 14 ቀን 2004 ዓም በማካሄድ ራሳቸው ሜትሮፖሊታን አቡነ ሚካኤል በአንድ ድምጽ ዐቃቤ መንበር ሆነው ተመ**ርጠዋል**፡፡ በዚህም መሠረት ፓትርያርኩ ተመርጠው በመንበራቸው እስኪቀመጡ ድረስ ሲኖዶሱን ይሰበስባሉ፡፡ በዚሁ ጉባኤ ላይ በቅዱስ ሲኖዶሱ የምርጫ ኮሚሽን ተመርጧል፡፡ የዚህ ኮሚሽን ተግባራትም

- ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና ከምእመናን ጉባኤ ዕጩዎችን መቀበል
- ከቅበላ እስከ ምርጫ ያለውን ሂደት ማስፈጸም ናቸው፡፡



www.danielkibret.com

ይህ ኮሚሽን አሥራ ስምንት አባላት ያሉት ሲሆን አባላቱም ዘጠኙ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ ዘጠኙ ደግሞ ከምእመናን ጉባኤ አባላት መካከል የሚሰየሙ ናቸው፡፡

ግብጽን ከአርባ ዓመታት በላይ አገልግለው ላረፉት ለብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ክብር ሲል ካረፉበት ቀን ጀምሮ እስከ ዓርባ ቀን ድረስ ዕጩዎችን ላለመቀበል ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኗል፡፡ ይህም ሚያዝያ 18 ቀን 2004 ዓም ይጠናቀቃል፡፡

ለፓትርክና ዕጩ መሆን የሚችሉት ቢያንስ የሚከተሉትን ያሟሉ ናቸው

- ዕድሜያቸው ቢያንስ ዐርባ ዓመት የሞላቸው
- በገዳም ውስጥ ቢያንስ አሥራ አምስት ዓመታት የኖሩ ደናግል መነኮሳት
- ሀገረ ስብከት የሌላቸው
- ነውር ወይንም ነቀፋ የሌለባቸው
- የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት በሚገባ የተማሩ

አንድ ዕጩ ዕጩ ለመሆን ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል በስድስቱ ወይንም ደግሞ ከምእመናን ጉባኤ አባላት መካከል በአሥራ ሁለቱ መጠቆም አለበት፡፡ ይህም ጥቆማ ያረፉት አባት ካረፉበት ቀን ከአርባኛው ቀን በኋላ እስከ ስድሳኛው ቀን ሊከናወን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ በቅዱስ ሲኖዶሱ አስቀድሞ በወጣው ሕግ መሠረት ለዕጩነት የሚያበቃቸውን መሥፈርት የሚያሟሉትን አባቶች ኮሚሽኑ ሲቀበል ይቆያል፡፡

በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ሚደዲያው፣ ካህናትና መምህራን ታላቅ ሚና አላቸው፡፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ዓይነት አባት እንደሚያስፈልጋት ሃሳብ በመስጠት፡፡ መራጮች ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በመምከር አስተዋጽዖ ያበረክታሉ፡፡ በአጥቢያዎችና በገዳማትም ጸሎት ይደረጋል፡፡ በሕዝቡም መካከል ማን የቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትርያርክ ቢሆኑ መልካም እንደሆነ ውይይትና ክርክር ይካሄዳል፡፡

በነገራችን ላይ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ፓትርያርክ ከጳጳሳት መካከልም ሆነ በገዳም ካሉ አባቶች መካከል ሊመረጥ ይችላል፡፡ ያረፉት ፓትርያርክ አቡነ ሺኖዳ ሀገረ ስብከት ከሌላቸው ጳጳሳት መካከል የተመረጡ ሲሆን፣ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ደግሞ ከገዳማውያን መካከል የተመረጡ ነበሩ፡፡ እስካሁን ሀገረ ስብከት ያለው ጳጳስ ፓትርያርክ ሊሆን አይችልም፡፡

አስመራጭ ኮሚቴው ጥቆማዎችን ከተቀበለ በኋላ በስድሳኛው ቀን የዕጩ መቀበያ ጊዜ ማብቃቱን ያውጃል፡፡ ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ ማለትም በሰባ አምስተኛው ቀን ሕጉን የሚያሟሉትን ዕጩዎች ለይቶ ስማቸውን ሕዝብ ሊያየው በሚችልበት ቦታና በሚዲያ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡ የዕጩዎች ስም



www.danielkibret.com

ለአሥራ አምስት ቀናት ይፋ ሆኖ ሲቆይ ዕጩዎችን በተመለከተ ቀሬታ፣ የተለየ ሃሳብ፣ መረጃ ወይንም ሌላ ነገር ያለው ሰው ለዕጩዎች ቅሬታ ተቀባይ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

የዕጩዎች ቅሬታ ተቀባይ ኮሚቴ አምስት አባላት ያሉት በቅዱስ ሲኖዶስ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡ ሦስቱ የኮሚቴው አባላት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የምእመናን ጉባኤ አባላት ናቸው፡፡

ይህ ኮሚቴ በቀጣዮቹ ሠላሳ ቀናት ውስጥ በዕጩዎች ላይ አሉ የሚባሉትን ቅሬታዎችና ለቅሬታዎቹም የሚሰጡ መልሶችን ሲያጣራና ሲወስን ይቆያል፡፡ ይህ ቅሬታ ግን መቅረብ ያለበት ድምፅ ለመስጠት ሥልጣን ባላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በኩል ብቻ ነው፡፡ ሌላ አካል መረጃ ወይም ቅሬታ ቢኖረው በእነዚህ አካላት በኩል እንዲቀርብ ማድረግ ይችላል፡፡

ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አባላት ማለት በቤተ ክርስቲያኒቱ የምርጫ ሕግ መሠረት ድምፅ ለመስጠት የተመረጡ አባላት ማለት ነው፡፡ እነዚህ ድምፅ የሚሰጡ አባላት የሚመረጡት በምርጫ ኮሚሽኑ በኩል ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በቤተ ክርስቲያኒቱ ይፋዊ አገልግሎት ያላቸው ካህናት(ማለትም ቦታ ይዘው ተመድበው የሚያገለግሉ ካህናት) ይወከላሉ፡፡ (በነገራችን ላይ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የካህናት ቁጥር ትንሽ ነው፡፡ እንደኛ 400,000 አድርገን አናስበው) እንዲሁም ከያንዳንዱ ሀገረ ስብከት አሥራ ሁለት የምእመናን ድምፅ ሰጭዎች ይመረጣሉ፡፡

በውጭ የሚገኙ አህጉረ ስብከትም እንደ ሀገር ቤቶቹ ሁሉ ካህናትንና ምእመናንን ይወክላሉ፡፡ ሀገረ ስብከት የሌላቸው አጥቢያዎችም አንድ ላይ ሆነው እንደ አንድ ሀገረ ስብከት ይታዩና ካህናትንና አሥራ ሁለት ምእመናንን ይወክላሉ፡፡

በፓትርያርኩ ምርጫ ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖራቸው

- የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት
- የቀድሞዎችና የአሁኖቹ የምእመናን ጉባኤ አባላት በሙሉ
- ከእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት የሚመጡ ካህናት
- ከእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት የሚመረጡ አሥራ ሁለት፣ አሥራ ሁለት ምእመናን
- አሁን ያሉና የቀድሞ ኦርቶዶክስ ሚኒስትሮች
- አሁን ያሉና የቀድሞ ኦርቶዶክስ የፓርላማ አባላት
- ኦርቶዶክስ የሆኑና በግብጽ የፕሬስ ማኀበር የተመዘገቡ ጋዜጠኞች ናቸው፡፡

ኮሚቴው የመራጮችን ዝርዝር ከተቀበለ በኋላ በትክክል መመረጣቸውንና በምርጫ ሕጉ መሠረት መመረጣቸውን እያረጋገጠ ይቀበላቸዋል፡፡ ይህም በስድሳኛው ቀን ይጠናቀቃል፡፡ ከስድሳኛው ቀን ጀምሮ



www.danielkibret.com

እስከ ሰባ አምስተኛው ቀን ድረስ ለአሥራ አምስተ ቀናት በመራጮት ላይ ቀሬታ አለን የሚል ቀሬታውን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን ለመራጭነት በተመረጠ አባል በኩል የሚቀርብ ቅሬታ መሆን አለበት፡፡ በሰባ አምስተኛው ቀን የመራጮች የመጨረሻ ዝም ዝርዝር ይፋ ይሆናል፡፡ የቅሬታ መቀበሉ ሂደትም ያቆማል፡፡

ለፐትርክና የተጠቆሙትን ዕጩዎች የማጣራቱ፣ የቀረበውን ቅሬታ አጣርቶ የመወሰኑ ሥራ እስከ አንድ መቶ ሃያኛው ቀን ድረስ ይከናወንና ያልቃል፡፡ በዚህ ቀንም ተጣርተው የቀረቡትን ከአምስት ያላነሱ ከሰባት ያልበለጡ ዕጩዎች ስም ዝርዝር የምርጫ ኮሚሽኑ ይፋ ያደርጋል፡፡ ከዚያ በኋላ በተመረጡት ዕጩዎች ላይ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በአንድ መቶ ሃምሳኛው ቀን ድምፅ ይሰጣሉ፡፡ የዚህም ውጤት በአንድ መቶ ሃምሳ አንደኛው ቀን ይፋ ይሆናል፡፡ በውጤቱም ከዕጩዎች መካከል ብዙ ድምፅ ያገኙት ሦስት አባላት ይፋ ይደረጋሉ፡፡

ሕዝቡም የሦስቱ አባቶች ስም ይፋ ከሆነ በኋላ በሚገኘው የመጀመርያው እሑድ  በመጨረሻዎቹ ሦስት አባቶች ስሞች ላይ ጸሎት ለማድረግ በቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ይሰበሰባል፡፡ በዚያ ቀን የሦስቱም አባቶች ስሞች በወረቀት ተጠቅልለው በመንበሩ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ጳጳሳቱ፣ ካህናቱና ምእመናኑ በአንድነት በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ በየቤተ ክርስቲያኑም ጸሎት ይደረጋል፡፡

ጸሎቱ ሲፈጸም አንድ ሕፃን ከሕዝቡ መካከል ይጠራና ዓይኑን በጨርቅ ተሸፍኖ በመንበሩ ላይ ጸሎት ከሚደረግባቸው ስሞች አንዱን ያነሣል፡፡ እርሱ ያነሣውን ስም የምርጫው ኮሚሽን ሰብሳቢ አንድ መቶ አሥራ ስምንተኛው ፓትርያርክ መሆናቸውን ያውጃል፡፡

እያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት የሚካሄድበት ቀን ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና ከአስገዳጅ ነገሮች አንፃር ሊቀየር እንደሚችል መግለጫው ያመለክታል፡፡ ግብፃውያን ግን በመስከረም 2005 መጨረሻ አካባቢ አዲስ አባት እንደሚያገኙ ተስፋ አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያውያንስ?